እስቲ ተመኙ

ከሁነቶች፣ ከነገሮች፣ ከክስተቶች የሆነ ነገር ተመኙ ብትባሉ ማንን መሆንን ትመኙ ነበር ወዳጆቼ። ምኞት አይከለከልምና እኔ ግን ተመኘሁ።

ከዘመናት ያንን የረሱሉን ዘመን ተመኘሁ፤ በርሳቸዉና በሶሐቦቻቸው ዘመን በኖርከና ከነርሱም ጋር በሆነኩ ብዬ ተመኘሁ። ከወራትም ረቢዕን ሆኜ ብሆን ኖሮ ብዬ ተመኘሁ። እጅግ የተከበሩት ነቢይ የተወለደቡት ወር ነዉና። ከቀናት መካከል መሆንን ተመኝ ብባል ኖር ጁሙዓ መሆንን ተመኘሁ፤ አላህ ለሙስሊሞች የመረጠው የሳምንቱ ታላቅ ቀን ነዉና። ከሶሐቦች መካከል አንዱን መሆን ተመኝ ብባል ሁሥማንን መሆንን ነበር የምመኘው እጅግ ትሁት ዐይናፋር ሰው ናቸዉና። ዐይናፋርና ረጋ ያለው ሰው እወዳለሁና። ከወቅቶች መካከል አንዱን መሆንን ምረጥ ብባል ዐደይን መሆን ነበር የምሆንላችሁ ተስፋ በልባችሁ እንዲሞላ አደርጋለሁና። ከመልኮች መካከል አንዱን ተመኝ ቢሉኝ አረንጓዴን ነበር የምመኘው፤ የጀነት ሰዎች ልብስ ቀለም ነዉና። ከከተሞች መካከል አንድ መርጠሀ ተመኝ ቢሉኝ መካን ነበር የምመኘው፤ ሐበ.ቢ ተወልደዉበታልና። ከቋንቋ መካከል የምትወደዉን ተመኝና ሁን ብባል ዐረብኛን መሆንን ነበር የምመኘው ፤ የጀነት ሰዎች ቋንቋ ነዉና። ከአባቶች መካከል ማንን ትመኛለህ ቢሉኝ አባቴን መሆን ነበር የምመኘው፤ ብርቱ የዲን እና የሥራ ሰው ናቸዉና። ከባህሪዎች መካከል አንዱን ምረጥና ሁን ቢሉኝ ፈገግታን ነበር የምሆነው፤ የሰዎችን መንገድ አበራለሁና። እንደማን ጀግና መሆን ትመኛለህ ብለው ቢጠይቁኝ አባ ዑበይዳን ነበር የምመኘው፤ ነቢዩም ሶ.ዐ.ወ. የሱ ዓይነት ብዙ ጀግና ተመኝተዋልና። ከቦታዎች መካከል አንዱን ተመኝ ብባል መስገድ መሆንን ነው የምመርጠው የነፍስ ስክነትን መገኛ ቦታ ነዉና። ከሚሰሠጡ ነገሮች አንዱን ምረጥ ብባል ትዕግስት ነበር የምመርጠው የሰው ልጅ ከተሠጠው ነገር ሁሉ ትልቁ ነዉና። ከሀብት መካከል ምረጥ ብባል ሙበቃቃትን ነበር የምመርጠው ከሙበቃቃት የበለጠ ሀብት የለምና። ከአፍቃሪዎች መካከል አንደማን መሆን ትመኛለን ኡሙ ሰለማን ታስቀናኛለች፤ አቡሰለማን እንደወደደችና እንዳከበረችው ዘልቃለችና። ከርሱ ሞት በኋላ ሌላ ላለማግባት ብዙ አንገራግራለችና። ከልጅ መካከል እንደማን መሆንን ትመኛለህ ቢሉኝ ፋጢማን ነበር የምሆነው አባቷ ረሱላችን በጣም ይወዷት ነበርና። ከሰዓታት መካከል ምረጥ ብባል ከለሊቱ ነዐ ሰዓትን ነበር የምመርጠው ብዙዎች የማይነቁበት፤ ወደ አላህ የመቃረቢያ ፀጥ ያለ ጊዜ ነዉና።

ዲን የማይመስል ነገር ...

"ይሄ ነገር ዲን አይመስለኝም::" አለ አንድ ስለዲኑ ብዙም ዕውቀት የለለው ሰው:: በሆነ ሰርግ ላይ በመድሕ እና በመንዙማ ሥም የሚያረገዉን ግጥፈራና ጠጣ ጠጣ ሲይዮ ነበር:: እውነት ነው፤ አላህ መጠነኛ የኢማን መንፈስ ያላበሰው ሰው እንኳን ዲንን ዲን ካልሆነው ነገር መለየት አያቅተዉም::

ዲን መንፈስ፣ ክብር፣ ሕይወት፣ ክብደት እና ሞገስ አለው:: ዛሬ ግን ብዙዎች የዲኑ አስኳልና ሥጋዉን ትተው ዉጫዊው ቆዳው ላይ አተኩረዋል:: ለብልግጉልግጉ ነገር እጅ ሠጥተው ዲንንም ሞገስና ክብር ያጣ ባዶ ቆርቆሮ አድርገዉታል::

ደጋጎች አንዳንድ ነገሮች ፍቱድ እንኳን ቢሆኑ ከመሰመር ያሰወጣሉ በሚል ጥራቻ የከልከል ታርጋ ለጥፊዉባቸው ወደ ዲኑ ሰርገው እንዳይገቡ መንገድ ይዘጉባቸው ነበር:: ሐራምን ፍራቻ ብለው ሐላል የተዉም እጅግ ብዙ ናቸው:: ይህን የሚያደርጉት አላህን ስለሚፈሩ ነው:: አላህን የሚፈራ ሰው ምን ይሆናል ብሎ በኃጢኣት ድንበር ዙርያ ሊይሸከረከርም:: አንዳንድ ውለሞቻችን በዲንም ሆነ ዱንያዊ ጉዳይ ላይ ፈትዋቸዉን የሚያጠብቁት ወደው ሊይደለም:: አማኙ እንደባለቤት አልባ መለቀቅ ስለሌለበት ነው:: በተለቀቅን ቁጥር ጥፋታችን የሚበዛ ስለመሆኑ የምናየው ያለ ነው:: ሲያግራሩል በጥሩ ጎኑ ከመጠቀም ይልቅ መወደቂያችን እናደርገዋለን:: ያግራሩለት ሰው በተግራራለት ቦታ ላይ አይቆምም፤ ይበልጥ ወደታች እየወረደ ይሄዳል:: እስት በዚህ ዙርያ በቅንነት ራሣችንን እንፈትሽ:: ዛሬ ላይ እንኳን ለቀኸው ከዲኑ ለመውጣት ሰበብ ፈላጊ ብዙ ነዉና::

አንዳንድ የምናከብራቸው ዉለሞች ይፈቀዳል ብለው በቅንነት ለነሺዳ ተከራከሩ:: አጋጣሚዉን የተጠቀሙ ወጣቶች ነሺዳን ቅልጥ ያለ ሙዚቃ አድርገዉት አረፉ:: ዛሬ ላይ ብዙ ሰው ነሺዳን ይሰማል፤ ቁርአንና ወዕዕ ማዳመጥን ትቷል:: ምክንያቱም በነርሱ ቦታ እነኚህ ገብተዋልና:: አንዳንድ ጠንካራ አማኞች ሙስሊሞች ዲናቸዉን ከፍ አርገው አንዲይዙ የሚመከሩት ወደው አይደለም:: ሰዎች በተውሒድ ጉዳይ ችላ የተባሉ እንደሆነ ለሺርክ ይጋለጣሉ:: በሱንና አብዝተው ካልተመከሩ ወደ ቢድዓ ያዘነብላሉ:: በቁርአን ነገር አደራ ካልተባሊ ነሺዳንና ሙዚቃን የዕለት ዉሏቸው ያደርጋሉ:: እንደኔ እንደኔ ዛሬ ላይ መንገድ ሊዘጋባቸው የሚገቡ ፍቱድ ነገሮች በርካታ ናቸው:: አላህ በሐላሉና በሚወደው ነገር ያብቃቃን:: አሁንም የሚያድነን ቁርአን እና ሱንና ብቻ ነው:

የፅናት ተምሳሌቷ እመት ዓኢሻ

ከሚገርመኝ የሕይወት ታሪኮች መካከል አንዱ የአናታችን የነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. የአሙት ዓኢሻ (ረ.ዐ.) ታሪክ ነው። በ13 ዓመቷ ነበር ያገባችው። ገና በ18 ዓመቷ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ተለዩዋት። የሚወዷትና የምትወዳቸው ባለቤታቸው ወደ አኺራ ተሻገሩ። አሥር ዓመት እንኳን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር አልኖረችም።

አዎ ዓኢሻ (ረ.ዐ.) ገና በአፍላ ወጣትነቷ ነበር ያዉም በእጅጉ የምትወዳቸዉን ተወዳጅ ባለቤቷን ያጣችው። በትዳር ዘመኗ ልጅ አልወለደችም። የሚገርመው "ልጅ ይኖረኝ ዘንድ ዱዓ አድርጉልኝ" ብላ ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ጠይቃለች የሚል ሐዲሥ አልተገኘም። ከርሣቸው ህልፈት በኋላ ሌላ ሰው ሳታገባ 47 ዓመታትን ብቻዋን ኖረች። ዓኢሻ ልጅ ባይኖራትም "ኡሙ ዑበደላህ" የዑበደላህ እናት በመባል ትጠራ ነበር።

እናት ዓኢሻ (ረ.ዐ.) ትልቁ ትኩረቷ መንፈሳዊ ነበር። ስለ ዓለማዊ ሕይወት ግድ አልነበራትም። በአላህ ከፍ‌ፍል ቅር አላላትም። መሉ ሕይወቷ በዒባዳ፣ በዕውቀትና በጂሃድ የተሞላ ነው። ትላልቅ ሶሐቦች ሷሚር ከሷ የዲን ትምህርት ተምረዋል፣ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችን(ፈትዋ) ለታላላቅ ሊቃዉንት ታስረዳ ነበር።

አህቴ አስቲ አስተዉይ። ከአሙት ዓኢሻ ረ.ዐ. ሕይወት ብዙ ብዙ ነገር ትማርያለሽ። መከልከል በደል ቢሆን ኖሮ የነቢዩ ሚስት የሆነችው ዓኢሻ ልጅ የሌላት በመሆኑ ተበድላለች ማለት እንችል ነበር። ግና አይደለም። አላህ ፍትሃዊና ምክንያታዊ የሆነ ጌታ ነው። ነገሮችን ለምን ዓላማ እንዳደረገ አሱ ያውቃል። አላህ ሰዎችን ምድር ላይ አሱ በሻው መልኩ ሊያኖራቸው ይችላል። ወደ ዱንያ ባዶ እጃቸዉን መጥተው ባዶ እጃቸዉን የሚመለሱ ብዙ ናቸው። ታዲያ ከነዚያ ብዙ ሰዎች መካከል አንዱ ብንሆን ሊገርመን አይገባም።

ዱንያ የፈተና ምድር መሆኗ ግልጽ ነው። ለማንም አላደላችም። ልጅ ስለጠፋ፣ ትዳር ስለጠፋ፣ ቤት ስለጠፋ፣ መኪና ስለጠፋ፣ገንዘብ ስለጠፋ ... ሕይወት አትቆምም ትቀጥላለች። አላህ በደለን ለሸይጧን መጥፎ ሀሳብና ጥርጣሬ በር አትስጠ፤ መገቢያ ቀዳዳዎችን አትከፈቱ። ከዚያ ይልቅ ቀልባችሁን አረጋጉ። አላህ በሚወደው ነገር ላይ አተኩሩ። አሱ ለሚወደው ነገር ትኩረት ስጡ። ሁሉን የሚሠጥ አላህ ነው።

ባሮቹን አታሳዝኑ ...

"ምን ሆንሽ?" ሲላት

"ጓደኛዬ ስለከፋት ከፍ.ዮኛል።" አለችው።

ለጓደኛ፣ ለወንድም እህት መከፋትና መታመም ከኢማን ነው ብንልስ።

በተለይ ለተበደለ ሰው መታመም የሙእሚን ባህሪም ነው በርግጥ።

ሙእሚን እንደ እንድ ሰውነት ነው:: አንደኛው የሰዉነት ክፍል ሲታመም ሌላኛዉም ይታመማል:: በህመምና በትኩሳትም እንቅልፍ ያጣል::

አንዳንዴ የሆነን ሰው ስንጎዳ አንድ ሰው ብቻ የምንጎዳ እንዳይመስለን:: ሳናስበው ጨምረን የምንጎዳቸው ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ጓደኛዉን እንጎዳለን፣ ቤተሰብ ልንጎዳ እንችላለን፣ ወንድም እህት ልንጎዳ፣ ወዳጅ ዘመድ ልንጎዳ እንቸላለን። በዚያ ሰው መጎዳት የተነሳ እነኚህ ሁሉ ያዝኑብናል፣ እነኚህ ሁሉ ይከፉብናል። አንዳንዴ እኛ ሳናውቅ ግፋችንን እና በደላችን ብዙ ሰው ዘንድ የሚደርስበት ሁኔታ አለ::

ሰው ብቻ አይደለም:: መላእክት ጭምር በሙእሚን መበደል ይከፋሉ፣ ይቆጣሉ፣ ያዝናሉ፣ ይራገማሉ። አላህ ለባሮቹ ይቆረቆራል፤ ባሮቼን አታሰቸግሩ ብሏል።

ባሮቹን ከማሳዘንና ከማስከፋት ተጠንቀቁ። የአላህን ወዳጅ መንካት ከአላህ ጋር ጦርነት እንደማወጅ ነው::

ስትተኙ ንፁሕ ሁኑ ...

በዉዱእ መተኛት ብዙዎቻችን የተዘናጋንበት ሱና ነው። ወዳጄዋ በዉዱእ መተኛት ቢያቅትህ እንኳን ንፁህ ልብ ታቅፊህ ተኛ:: ንፁህ ልብስ ለብሰህ ጥሩ የምታዉድ ሆነህ ተኛ ይላሉ ደጋጎች። ማን ያውቃል ሊሊት ላይ መላእክት ይሁን ሌላ የምታከብረው ወዳጅና እንግዳ ብህልምህ ይመጣ ይሆናል። ንጽሕና ከሸይጧን መራቅ ለመላእክት መቅረብ ነው።

አናም እንደ ኩንታል ደራርበህ ፍየል ፍየል እየሸተትክ አትተኛ።

ዛረትኩሙል መላኢካ ቲስበሑ ቢኸይር!!

ለምን እኔን ብቻ ...

አላህ ሱ.ወ.ዱንያ የፈተና አገር አድርጎ ፈጠራት። ፈተናዎች አላህ ማናችን ታጋሽና እውነተኛ እማኝ እንደሆነን የሚያበጥርበት ወንፊት መሆናቸው አሙን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎቹ እኛ ላይ የሚደርሱብን ችግሮችና ፈተናዎች የሸይጧን መጫወቻ ካርዶች ናቸው ብዬ አስባለሁ። የሆነ ችግር በኛ ላይ በተፈጠረ ቁጥር ሸይጧን አነርሱን ይመዝና ኢማናችንን ጥርጣሬ ዉስጥ ይከታል። የምንወደዉን አምላካችንን አላህ ሱ.ወ. ከዉስጣችን ሊያወጣ ይጥራል። በዲናችን ላይ ወሸንብር ይፈጥርብናል። የቁናችንን ያፈታብናል። እኛም ሰው ነንና መከራ ሲበዛብን እንደከማለን። ችግር ሲደራረብ እንነጫነጫለን። አንዳንዴም ሙተንፈሳችን እይቀርም መቸስ...። በዚህም የተነሳ ራሳችንን የጠየቅንባቸው ጊዜያትም በርካታ ናቸው። እየሰገድኩለት፣ እየፆምኩለት፣ እየለመንኩት .... አላህ ለምን በኔ ላይ ጨከነ ... ለምን እኔን ብቻ ፈተነ ... እኔ አላህን ምን አድርጌው ነው ... ስንል እንጠይቃለን። አንዳንዴ ከዚህም ከፍ ያሉ ለመናገር የሚከብዱንን ሀሳቦች ጭምር በዉስጣችን እናነሳለን።

ወዳጆቼ! መጀመርያ ላይ ማወቅ ያለብን ትልቁ ነገር ምድር ላይ ያስገኘን አምላካችን አላህ ሱ.ወ. ፍጹም ፍትሃዊ እና ጥበበኛ የሆነ ጌታ እንደሆነ አንርሳ። በፍትሁ እና በጥበቡ ሰዉን በሻው መልኩ አኖረ። አንዱን በሙሉ አካል ፈጠረ። ሌላዉን አካሉን አጎደለ። ላንዱ ሠጠ ለሌላው ነሳ። ላንዱ ሸለመ ለሌላው ከለከለ። አሱ ጠፍጥፎ በሠራው የሰው ልጅ ላይ የፈለገዉን ነገር ቢያደርግ መብቱ ነው። ደግሞም ፈተና ስንል ለኛ መልካም መስሎ የሚታየን ነገር ብቻ አድርጋችሁ አታስቡ። በድህነትና በበሽታ ዉስጥ ፈተና እንዳለ ሁሉ በተድላም በፀጋም፤ በጤናም በሀብትም፣ በማግኘትም በማጣትም ዉስጥ ፈተና አለ። በድህነት የተፈተነ እንዳለ ሁሉ ሀብትም ፈተናው የሆነ ብዙ ነው። ሀብት ፈተና የሚሆነው አላህ በሚፈልገው ነገር ላይ ያላዋለነው እንደሆነ ነው። በሽታ ፈተና ቢሆንም ጤናም ፈተና ሆኖ ስንቱን ከዲኑ አሰወጥቷል መሠላችሁ!።

አንዳንድ ጊዜ ድህነት የማንችለው ፈተና ነዉና ሀብት ስጠን ብለን አላህን ልንለምነው እንችላለን። ግና ቢከለክለን ሙቡቱ ነው። እኛም በርሱ እጅ ያለን ነገር የመነጠቅ ጉልበት የለንም። ጤና፣ ትዳር፣ ሰላም፣ ልጅ፣ ሀብት... የርሱ ናቸው። ከርሱ ካዝና የሚለቀቁ ፀጋዎች ናቸው። የኛ ድርሻና ግብረመልስ መሆን ያለበት ሲሰጠን ማመስገን፤ በሠጠኸን ነገር አትፈትነን ማለት ነው። ሲከለክለንም ማመስገን፤ መልካሙንና ጠቃዉን ነገር ስጠን ብሎ መለመን ነው።

በዚህ ሁሉ መሃል አንድ አሳቤ እናስተካክል። የምንሰግደዉና የምንያመው አላህ የሆነ ነገር እንዲሠጠን አይደለም። ባሮቹ ስለሆንን እሱን ፈጣሪያችን ማምለክም ግዴታችን ስለሆነ ነው። ወደዚህ ምድር ስንመጣም ለርሱ አምልኮ የተፈጠሩ የአላህ ባሮች ሆነን እንጂ ሌላ አይደለም። ቢሠጠንም ባይሠጠንም እናመልከዋለን። ከዚህ ባለፈ ግን አኛ እናገልግልህ አንተ ከፈለን ማለት ንግድ ነው የሚሆነው። ከአላህ ጋር የምንኖረው በጌታና በባርያ ግንኙነት እንጂ በመስጠት መመለስ መርህ አይደለም።

አኛም ሆንን ፍጥረተዓለሙ ሁላ የርሱ ሥራት ነው። አኛም በግዛቱ ዉስጥ የምንኖር ደካማ ፍጡራን እንጂ ሌላ አይደለንም። ቀና ብለን እሱን ለመናገር፣ ለመውቀስም፣ ለመተቸትም ሥልጣኑም አቅሙም የለንም። በርሱ እንጠየቃለን እንጂ አኛ አሱን አንጠይቅም። እንነመገማለን እንጂ አንገመግመዉም። እርሱ የሻዉን ሠሪ ብቻዉን ቀሪ ነው ጌታዬ። ሩሓችን፣ ጀሰዳችንና ሁለመናችን እንደፈለገ ቢያደርግ መብቱ ነው። አኛ የርሱ ወደርሱም ነንና። ከርሱ ተነሳን ወደርሱ እንመለሳለን።

ስለዚህ ወዳጆቼ! አላህ አኛን የፈጠረበትን ዓላማ ጠንቅቀን ካወቅን በሱ ላይ አብዝተን መጽናት ነው የሚገባን። ካላወቅን ደግሞ ሥርዓት መያዝ፣ አደብ ማሳድረግ የኛ የባሮቹ ሁኔታ መሆን አለበት። ባርያ ጌታው ፊት አይናገርም። ፍጡር ፈጣሪው እንዳረገው ነው የሚሆነው።

ወዳጆቼ! ትናንትም ሆነ ዛሬም፣ ወደፊትም ጭምር መልስ ያጣንላቸው ነገሮች ዉስጣችን በተፈጠሩ ቁጥር ብዙ ማሰብ ማሰላሰል የለብንም። ጉዳዩን ወደ አላህ ሱ.ወ. በመመለስ መቋጫ ልናበጅለት ይገባል። ሁለመናችን ለርሱ ማስረከብ ይገባል።

እኛ አመንንም አላመንንም አላህን ሱ.ወ. የምንጎዳው ምንም ነገር የለም። ፍፁም በሆነ መልኩ ሰጥ ለጥ ብለን ብናምንና ብንገዛው ግን ተጠቃሚዎቹ አኛው ነን። አላህ በሩቅ የሚያምኑትን ይወዳል።

በመጨረሻም ጊዜው ቢረዝምም፣ የቱን ያህል ከባባድ ፈተናዎች ዉስጥ ቢያልፉም አላህን ፈሪዎች፣ ታጋሾችና የኢማን ባለቤቶች ማሸነፋቸው እንደማይቀር አትጠራጠሩ። አላህ ሱ.ወ. መጨረሻቸው ያማረ እንደሚሆን ቃል ገብቷልና። ወልዓቂበቱ ሊልሙተቂን።